## የተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፈልባቸው የሚችሉ ሌሎች አቅርቦቶች

የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ በየዕለቱ የሚፈፀም ሳይሆን በወር አንድ ጊዜ ተጠቃልሎ የሚከፈል የታክስ ዓይነት ነው፡፡ ታክሱ ሊከፈልባቸው የሚገባ ሌሎች አቅርቦቶች ከሚባሉት የሚከተሉትን በምሳሌነት ማየት ይቻላል፡፡

- ለሠራተኞች በቅናሽ የሚሸጡ ዕቃዎች፣ ምግቦች ወዘተ. .፣
- የንግድ ሥራ ንብረቶች ሽያጭ/ ለምሳሌ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች፣ ለንግድ ሥራ የሚውሉ ተሽከርካሪዎች፣ መሳሪያዎች ወዘተ. .፣
- ዕቃዎችን ለሌላ ሰው ማከራየት፣
- ለጓደኞችና ለንግድ ተወካዮች የሚሰጡ ስጦታዎች፣
- የንግድ ሥራው ባለቤት ወይም ቤተሰቡ ለራሳቸው ጠቀሜታ ከንግዱሥራ ላይ የሚወስዷቸው ዕቃዎች፣
- ሌላ ሰው በመወከል ከሚካሄድ ሽያጭ የሚገኝ ኮሚሽን፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፈልባቸው ከሚችሉት አቅርቦቶች በአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## የገንዘብ ክፍያን ያስከተሉ ባይሆኑም የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲታሰብ

አንድ ሰው ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ከንግድ ሥራው ላይ በስጦታ መልክ ለሌላ ሰው ሲያበረክት በወቅቱ ባለው የዕቃዎቹ ወይም የአገልግሎቱ የገበያ ዋጋ ላይ በመመስረት የተጨማሪ እሴት ታክሱን ማሰብ ይኖርበታል፡፡  በተመሳሳይ ሁኔታም አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር የዕቃ ልውውጥ ቢያካሂድ ለለውጥ ባቀረበው ዕቃ ሙሉ የገበያ ዋጋ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክሱን በማሰብ የምርት ውጤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ ይሆናል፡፡

## የግብዓት ታክስ (Input **Tax**)

አንድ ሰው የሚገዛቸው ብዙዎቹ ዕቃዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ የታሰበባቸው እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ገዥው/ሸማቹ/ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ከሆነ ለንግድ ሥራው ባከናወናቸው ግዥዎችና ወጪዎች ላይ የተከፈለውን የግብዓት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ ሊጠይቅ/ሊያስብ/ ይችላል፡፡ የግብዓት ታክስ በጥሬ ዕቃዎች ግዥ ወይም ዕቃዎችን መልሶ ለመሸጥ በተደረገ ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብቻ ሳይሆን የሚከተሉትንም ይጨምራል፡፡

- ለንግድ ሥራው የተገዙ የቢሮ ዕቃዎችን፣
- ከንግዱ ሥራው ጋር በተያያዘ ለዕቃ ማጓጓዣ የተገዙ ተሽከርካሪዎችን፣
- ለንግድ ሥራው ተግባር የዋሉ የቴሌፎን ወጪዎችን፣
- ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ ለጠበቆች ወይም ለአካውንታንቶች ለተፈጸሙ ክፍያዎች ወዘተ ናቸው፡፡

ሆኖም ይህ ሁኔታ ቢኖርም አንድ ሰው ለሌላ ሰው የንግድ ድርጅት ለሚገዛው ዕቃ የተከፈለን የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የራሱን መኖሪያ ቤት ለማሟላት በፈፀመው ግዥ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ /ተመላሽ/ ወይም ክሬዲት ሊያዝለት አይችልም፡፡ በዚህ ሁኔታ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ የግብዓት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተብሎ ሊታሰብ አይችልም፡፡

## ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሆኑ አቅርቦቶችን

ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሆኑ የዕቃና የአገልግሎት አቅርቦቶችን የሚያመርት ወይም አገልግሎቶችን የሚያበረክት ማንኛውም የንግድ አንቅስቃሴ ለግብዓት በተከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ /ተመላሽ/ ለመጠየቅ አይችልም፡፡

**ይቀጥላል፡፡**